

••• •• •••• ••••• ••• ••• •••• ••••



••• •• ••••• ••••



••• •• ••••••

፭፮ ባሕታዊ ኣባ ጢሞቴዎስ

(ABBA TIMOTHY THE HERMIT)

በአንድ ወቀት ኣባ ጳፍናቴምስ (Abba Paphnatious) እንዲህ አለ፡-

"የተባረኩ ባሕታውያን አባቶችን ለማየት ወደ ምድረ በዳ የመሔድ ፍላጎት ነበረኝ። ... ስለሆነም የምበላውም ሆነ የምጠጣው ሳይኖረኝ በምድረ በዳው ውስጥ ዐራት መዓልትና ዐራት ሌሊት ተጓዝሁ። ድንገት አንድ በኣት አየሁ፤ ስለሆነም ቀረብ ብዬ ገዳማዊ ባህል ነውና በሩን አንኳኳሁ፤ ግን ማንም አአልመለሰልኝም። እስክ እኩለ ቀን ድረስ ከመግቢያ በሩ ላይ ቆየሁ፤ ከዚያም "ባርከኝ አባ" እያልሁ ገባሁ። በጸጥታ የተቀመጠ አንድ መነኩሴ አየሁ፤ እናም እጁን ዘርግቼ ክንዱን ያገዘሁት። ልክ ክንዱን እንደያዝሁት ወዲያውኑ ተፈረካከሰና እንደ ትቢያ ሆነ። ... ለራሴ በመስቀል ምልክት አማተብሁ፤ ጸለይሁና ከዚያ ወጥቼ ሔድኩ።

ከዚያም ጥቂት እንደተጓዝሁ ወደ አንዲት በኣት አየመራ የወሰደኝን የሰው ዱካ አገኘሁ። አሁንም በሩን አንኳኳሁ፤ መልስ ግን የለም። ከበኣቱ መግቢያ በር አጠገብ ተቀመጥሁና ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፡ - "የዚች በኣት ባለቤት ወደየትም ይሒድ ተመልሶ ይመጣል፤ ስለዚህ እዚሁ ተቀምጬ እጠብቀዋለሁ።"

እኔም ፀሓይ እስክትገባ ድረስ ከመግቢያ በሩ አጠገብ እየጸለይሁ ቆየሁ፤ ከዚያም አንድ ሰው በመካከላቸው እየተራመደ አንድ የዜብራ መንጋ ከፉቅ አየሁ። ወደ እርሱ በተቃረብሁ ጊዜ ራቁቱን እንደነበረና ፀጉሩም

ልክ እንደ ልብስ ስውነቱን ሸፍኖት እንደነበር አስተዋልሁ። እርሱም መንፈስ እንደነበርሁ አስቦ ነበርና በጣም ፈርቶኝ ነበር፣ ስለሆነም በቅጽበት ቆመና መጸለይ ጀመረ። ወደ እርሱ ሒድኩና "አትፍራ አባ፣ እኔም የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ነኝና፣ መንፈስም አይደለሁም አጥንትና ሥጋ አለኝና" አልሁት። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እያወጣ መጥቀስ ጀመረ፣ ከዚያም ልባዊ ሰላምታ አቀረበልኝ። ወደ በላቱ አብራው ሒድኩና ጸለይን፣ ከዚያም አብረን ተቀመጥን። "የዚህን ምድረ በዳ ባሕታውያን አባቶች ለማየት በጣም አፈልግ ነበር፣ ስለዚህም እንተን በማየት ፍላጎቴን ስላሟላልኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ቅዱስ አባቴ ሆይ፣ አባክህ ታሪክህን ንገረኝ ..." አልሁት።

"እኔ እንደ ገደማዊያን ልማድ በእጅቼ እየሰራሁ በገዳም የምኖር መነኩሴ ነበርሁ። የምሠራውን ሁሉ ለአትመ ደካሞች፣ ለድሆችና ለእንግዶች አከፋፍል ነበር። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ከገዳሙ ውጭ ለራሴ በላት ሠራሁና በዚያች ውስጥ መኖር ጀመርሁ።

የመልካም ነገር ሁሉ ጠላት ዲያብሎስ ግን ከእኔ ሩቅ አልነበረም። እርሱም በሥራየ በቅናት ተነሣሣ። አንድ ቀን ብዙ ጊዜ የእጅ ሥራዬን በምትገዛኝ በአንዲት መነኩሲት አምሳል ወደ እኔ መጣ። ቀስ በቀስ በሁለታችን መካከል የተለየ ግንኙነትና መቀራረብ ተፈጠረ። እኔን ለማየት በማንኛውም ሰዓት በመጣች ጊዜ አንድ ቀን ከእርሷ ጋር ኃጢአት እስክፈጽም ድረስ አብረን እንቀመጣለን፣ አብረን እንበላለን፣ አብረንም እንጓዛለን። ...

በቀጣየቹ ስድስት ወራት ልቡናዬ ደንድኖ ነበር፣ በመጨረሻም አንድ ቀን ቁጭ ብዬ በመነኩሲቷ አምሳል ዲያብሎስ ባስቀመጠልኝ በዚህ ፈተና ተገረምሁ፣ በጣም አዘንሁ። በኃጢአቱ በመጸጸት መራራ ልቅሶን

አለቀስሁ። በዚያች ቅጽበት ሞትንና በኃጢአቱ ምክንያት የሚያገኘኝን መከራና ስቃይ አሰብሁ፣ ስለሆነም ጠንክር አልሁና ለራሴ "ከኃጢአትህ ተነሣና ወደ ምድረ በዳ አምልጥ፣ በዚያም እግዚአብሔር እንደሚምርህና ይቅር እንደሚልህ ተስፋ በማድረግ ስለታላቁ ኃጢአትህ የንስሓ እንባን አንባ፣ ባለማቋረጥም ወደ ጌታ ጸልይ!" አልሁ። ወዲያውኑ ተነሣሁና በአቴን ትቼ ወደ ምድረ በዳ ተንገዘሁ። በመጨረሻም እግዚአብሔር ከዚህ የሚያምርና ውብ የቱምር ዛፍ አጠገብ ወደምትገኝ ወደዚች ዋሻ መራኝ። ይህ የቱምር ዛፍ በዓመት ዐሥራ ሁለት ቅርጫት ቱምር ያፈራል፣ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት ምግቤ ይህ ብቻ ነው። ልብሴ ባለቀ ጊዜ እንደምታየው ስውነቴን ለመሸፈን ፀጉሬ ያድግ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ።"

እኔም ቅዱሱን ባሕታዊ አባት "መጀመሪያ ወደ ምድረ በዳ በመጣህ ጊዜ መከራና ችግር አጋጥሞህ ነበርን?" ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም እንዲህ በማለት መለሰልኝ፦ "አዎ፣ ብዙ መከራ ደርሶብኛል። ከሀመሜ ጽናት እና ከልቤ ጽኑ ሀዘን የተነሣ ብዙ ጊዜ ራሴን ወደ መሬት እወረውር ነበር፣ ብዙ ጊዜም እየሞትሁ እንደነበር አስብ ነበር። ለጸሎት መቆም እስኪሳነኝ ድረስ ሀመሜ ከባድ ነበር፣ ስለሠራሁት ታላቅ ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ እየለመንሁ ለዐራት ዓመታት ቀንና ሌሊት መጸለይና ማልቀሴን አላቋረጥሁም ነበር።

አንድ ቀን ሀመሜ እየባሰበት እየመጣ መሆኑ ሲሰማኝ ለራሴ እንዲህ እያልሁ አሰብሁ፦ 'ይህ ሀመም የረከሱ ሀሳቦቼና ፍላጎቶቼ ውጤት ነው፣ ስለዚህ ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔር እንዲፈውሰሽ ትፅግስተኛ ሁኚ።" ከዚያም መላ አካሉ በብርሃን የተሞላ ሰው ከፊቴ ቆሞ "ሀመምህ የት ላይ እንደሆነ አሳየኝ?" አለኝ። እኔም ወደ ጉበቴ ጠቁሜ አሳየሁት። እርሱም ቀስ ብሎ በእርጋታ እጁን ከሚያመኝ ቦታ ላይ አስቀመጠውና "አሁን ተፈውሰሃል፣ ግን ዳግመኛ እንዳትበድል። በጸሎትህ ትተሀና

ንቁ ሁን" አለኝ። ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ያለአንዳች ሀመም ኖርሁ።

እኔ ጳጵናቴዎስ ከእርሱ ጋር በበኣቱ ውስጥ መኖር የምችል ከሆነ ጠየቅሁት፤ እርሱ ግን "ተወዳጁ ወንድሜ ሆይ፣ ሁሉንም የሰይጣን ውጊያዎች መቋቋም አትችልም" በማለት መለሰልኝ። ከዚያም "አባ፣ እስከ አሁን ድረስ ስምህን አላወቅሁም" አልሁት። እርሱም "ስሜ ጢሞቴዎስ ይባላል፤ እባክህ በጸሎትህ አስበኝ" አለኝ።

በፊቱ በጉልበቴ ተንበርክኬ እንዲጸልይልኝ ጠየቅሁት። "ከቅዱሳን አባቶችህ ጋር አንድ ትሆን ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይባርክህ፤ ከጠላት ወጥመድም ያድንህ፤ መንገድህ ቀጥ ያለ ይሁንልህ፤ ሥራዎችህም እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ይሁኑልህ። ..." እያለ ጸለየልኝ።

ከጸለየልኝና ከባረከኝ በኋላ የባሕታዊውን የአባ ጢሞቴዎስን ሕይወት ለመኖር እየተመኘሁ በደስታ ተጥለቅልቄ ወደ በኣቴ ተመለስሁ።

ቤተ ክርስቲያናችን የባሕታዊ አባ ጢሞቴዎስን በዓል በየዓመቱ በተባረከው ወር በታኅሣሥ 23 ታከብራለች።

የቅዱሱ አባት የአባ ጢሞቴዎስ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።

